# የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

# የምግብ ማስተዋወቅ ቁጥጥር መመሪያ
# 359/2013

ታህሳስ 2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

1. መግቢያ ........ 2
2. ክፍል አንድ ........ 3
3. ጠቅላላ ........ 3
    1. አጭር ርዕስ ........ 3
    2. ትርጓሜ ........ 3
    3. ዓላማ ........ 5
    4. የተፈጻሚነት ወሰን ........ 5
4. ክፍል ሁለት ........ 6
5. ምግብን ስለ ማስተዋወቅ ........ 6
    5. ስለ ምግብ ማስታወቂያ አስነጋሪ ........ 6
    6. ስለ ምግብ ማስታወቂያ መረጃ ........ 6
    7. ስለ አጠቃላይ ክልከላ ........ 6
    8. አጋዥ መረጃዎች፣ ሽልማቶችና ሌሎች ሰነዶች ስለ መጠቀም ........ 7
6. ክፍል ሶስት ........ 7
7. ስለ ጨቅላ፤ ታዳጊ ህጻናትና ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ምግብ ማስታወቂያ ........ 7
    9. ስለ ጨቅላ ህፃን ምግብ ማስታወቂያ ........ 7
    10. ስለ ታዳጊ ህጻናት ምግብ ማስታወቂያ ........ 8
    11. ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅን ስለሚመለከት የምግብ ማስታወቂያ ........ 8
8. ክፍል አራት ........ 9
9. ስለ ተጨማሪ ምግቦች ማስታወቂያ ........ 9
    12. የተጨማሪ ምግቦች ማስታወቂያ ........ 9
    13. ስለ አልኮል መጠጥ ማስታወቂያ ........ 10
    14. በስፖንሰር ስለሚቀርብ ማስታወቂያ ........ 11
    15. ስለተካታች ማስታወቂያ ........ 11
    16. ማስታወቂያ አሰራጭ ኃላፊነትና ግዴታ ........ 11
    17. ስለ መረጃ ........ 11
    18. ስለ አፀፋ ማስታወቂያ ........ 11
    19. የመተግበር ግዴታ ........ 11
    20. ቅጣት ........ 11
    21. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች ........ 12
    22. የተሻረ መመሪያ ........ 12
    23. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ ........ 12
10. **እዝል 1** ........ 13

## መግቢያ

የምግብ ማስታወቂያ ስራ በሥርዓት ካልተመራ የሕብረተሰብን ጤና ሊጎዳ የሚችል በመሆኑ፤

የምግብ ማስታወቂያ ደረጃውን የጠበቀና ተአማኒነት ባለው መንገድ እንዲመራ በማስፈለጉ፤

የማስታወቂያ ወኪሎች፣ የማስታወቂያ አሰራጮች እና የማስታወቂያ አስነጋሪዎችን የሚያሰራጩትን የምግብ ማስታወቂያ በሚመለከት በመመሪያ መወሰን በማስፈለጉ፤

የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀፅ 55 (3) እና በደንብ ቁጥር 299/2006 አንቀጽ 98 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህ የምግብ ማስተዋወቅ ቁጥጥር መመሪያ ወጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የምግብ ማስተዋወቅ ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 359/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

በአዋጁና በደንቡ ላይ የተቀመጡት ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡

1. "ምግብ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የተሰጠው ትርጓሜ እንደተጠበቀ ሆኖ በምግብ አምራች ድርጅት ተመርቶ ከአንድ ክልል በላይ ወይም ለውጪ አገር ገበያ ሽያጭ የተዘጋጀ ምርት ነው፤
2. "የጨቅላ ህፃናት ምግብ" ማለት ከእንስሳ ወይም ከእጽዋት የሚገኝ ወተት ወይም ወተት መሰል ውጤት ሆኖ አግባብ ባለው የጨቅላ ህፃናት ምግብ ደረጃ መሰረት በፋብሪካ የተዘጋጀና ከውልደት እስከ ስድስት ወር እድሜ ላሉ ጨቅላ ህፃናት የንጥረ ምግብ ፍላጎትን ለሚሟላት የተዘጋጀ ምግብ ነው፤
3. "የታዳጊ ህፃናት ምግብ" ማለት ከእንስሳ ወይም እጽዋት የሚገኝ ወተት ወይም ወተት መሰል ውጤት ሆኖ አግባብ ባለው የህፃናት ምግብ ደረጃ መሰረት በፋብሪካ የተዘጋጀ ከስድስት ወር እስከ ሶስት አመት የሆነን ህፃንን ለመመገብ ተስማሚ እንደሆነ የተገለፀ ወይም በሌላ መልኩ ገበያ ላይ የዋለ ምግብ ነው፤
4. "ተጨማሪ ምግብ" ማለት ማንኛውም መደበኛ አመጋገብን የንጥረ ምግብ ፍላጎት ለማሟላት የሚዘጋጅ የንጥረ ምግብ ወይም ፊዚዮሎጂካል ውጤት ያላቸው የቫይታሚን ወይም የማዕድን ወይም የሌሎች ንጥረ ነገሮች በነጠላ ወይም በጣምራ የሚገኙበትና በተወሰነ መጠን እንዲወሰድ ታስቦ በካፕሱል፣ በእንክብል፣ በዱቄት፣ በፈሳሽ፣ በጠብታ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ የሚዘጋጅ የምግብ ዓይነት ነው፤
5. "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት በምግብ ንግድ ሥራ ላይ የሚሰማራ ድርጅት አስፈላጊውን ድርጅታዊ መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ በባለሥልጣኑ አካል የሚሰጥ የሥራ ፈቃድ ነዉ፤

6. "የምግብ ንግድ ድርጅት" ማለት በምግብ ማምረት፣ መላክ፣ ማስመጣት ወይም ጅምላ ማከፋፈል ንግድ ስራ የተሰማራ ድርጅት ነው፤

7. "የምግብ ማስታወቂያ" ማለት የምግብ ንግድ ድርጅቱ የምግቡ ሽያጭ እንዲስፋፋ ወይም ስም፣ አርማ፣ የንግድ ምልክት ወይም አላማ እንዲተዋወቅ በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሰራጭ የንግድ ማስታወቂያ ሲሆን የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያንና የግል ማስታወቂያን ይጨምራል፤

8. "የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ" ማለት የምግብ ማስታወቂያን ለማሰራጨት የሚያገለግል ሲሆን መገናኛ ብዙሃንን፣ የውጭ ማስታወቂያን፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የፖስታ፣ የኢንተርኔት ድረ ገፅ እና የፋክስ አገልግሎትን፣ ሲኒማን፣ ፊልምን፣ ቪዲዮ፣ በፖስተር በመጽሔትና በበራሪ ጽሁፍ ወይም መሰል የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድን ይጨምራል፤

9. "የማስታወቂያ አሰራጭ" ማለት በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የአየር ጊዜ፣ የሕትመት ሽፋን ወይም መሰል አገልግሎት በመስጠት ማስታወቂያ የሚያሰራጭ ሰው ነው፤

10. "የማስታወቂያ አስነጋሪ" ማለት በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት ማስታወቂያ የሚተዋወቅለት ሰው ነው፤

11. "መገናኛ ብዙሃን" ማለት የሕትመት መገናኛ ብዙሃን እና የብሮድካስት አገልግሎትን ያካትታል፤

12. "የሕትመት መገናኛ ብዙሃን" ማለት በጠቅላላው ኅብረተሰብ ወይም በአንድ በተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍል እንዲነበብ ታስቦ የሚሰራጭ ማንኛውም ሕትመት ሲሆን ጋዜጣን፣ መጽሔትን፣ የማስታወቂያ መፅሀፍ ወይም የሎው ፔጅን፣ የስልክ ቁጥር ማውጫ ወይም ግሪን ፔጅን ያካትታል፤

13. "የብሮድካስት አገልግሎት" ማለት የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ሥርጭት አገልግሎት ነው፤

14. "የውጭ ማስታወቂያ" ማለት በቢልቦርድ፣ በኤሌክትሮኒክ ስክሪን ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል፣ በሕንጻ ወይም በማናቸውም ስትራክቸር ወይም በትራንስፖርት ተሽከርካሪ ላይ የሚፃፍ ወይም የሚለጠፍ፣ በተንጠልጣይ ነገር፣በፖስተር፣በስቲከር፣ በብሮሸር፣ ሊፍሌት ወይም በራሪ ወረቀት፣ በድምጽ ካሴት፣ በድምፅ ማጉያ መሳሪያ እና በሌላ መሰል ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሰራጭ ማስታወቂያ ነው፤

15. "ስፖንሰር" ማለት ፕሮግራምን ወይም የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ገንዘብ የከፈለ ወይም የክፍያ ቃል የገባ ሰው ነው

16. “ተካታች ማስታወቂያ” ማለት ብሮድካስተሩ ገንዘብ የተቀበለበትን ወይም ጥቅም ያገኘበትን የማንኛውንም ሰው ምርት፣ አገልግሎት ወይም መሰል መልእክት በተዘዋዋሪ ለማስተዋወቅ በፅሁፍ፣ በድምጽ ወይም በምስል ከአንድ ፕሮግራም ጋር የተካተተ ማስታወቂያ ነው፤
17. “የአፀፋ ማስታወቂያ” ማለት በህዝብ ዘንድ የተፈጠረውን የተሳሳተ አመለካከት ለማቃናት ወይም ለጉዳት የተጋለጠውን ወገን መብት ለማስጠበቅ የሚሰራጭ ማስታወቂያ ነው፤
18. “ልዩ ሱቅ” ማለት አግባብ ባለው አካል በሰጠው ፈቃድ መሰረት የተለዩ የምግብ ምርቶችን ብቻ የሚሸጥ የንግድ ሱቅ ነው፤
19. “የጤና ተቋም” ማለት የጤና ማበልፀግ፣ የበሽታ መከላከል፣ ማከምና መልሶ ማቋቋም ስራዎችን ወይም የመድኃኒት ንግድ ስራን ወይም አገልግሎት የሚያከናውን ማንኛውም የመንግስት ወይም የግል ተቋም ነው፤
20. “የጤና ባለሙያ” ማለት የሰውን ጤና ለመጠበቅ ወይም አገልግሎት ለመስጠት አግባብ ባለው አካል እንደ ጤና ባለሙያ የተመዘገበ ሰው ነው፤
21. “ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅ” ማለት 18 አመት ያልሞላው ልጅ ማለት ነው፡፡
22. “አግባብ ያለው አካል” ማለት የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ነው፤
23. “አዋጅ” ማለት የምግብ፣የመድሀኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 ነው፤
24. “ደንብ” ማለት የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 299/2006 ነው፤
25. “ባለሥልጣን” ማለት የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፤
26. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
27. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፤

3. ዓላማ

በሀገራችን የሚሰራጩ የምግብ ማስታወቂያዎችን ትክክለኛነት በማረጋገጥ የህብረተሰቡን ጤና ማስጠበቅ፤

4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሀገራችን በሚሰራጩ የምግብ ማስታወቂያዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ምግብን ስለ ማስተዋወቅ

5. ስለ ምግብ ማስታወቂያ አስነጋሪ

ማንኛውም የማስታወቂያ አስነጋሪ ድርጅት ለሚያስተዋውቀው ምግብ ከባለስልጣኑ ምግብን ለማምረት ወይም ለመላክ ወይም ለማስመጣት ወይም ለማከፋፈል አዲስ ወይም የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሲኖረውና በተጨማሪም የታዳጊ ህጻናትና ተጨማሪ ምግቦችን የሚያስተዋውቅ ከሆነ ደግሞ ምግቦቹ በባለስልጣኑ ተመዝግበው ፈቃድ ያገኙ መሆናቸው መረጋገጥ አለበት፡፡

6. ስለ ምግብ ማስታወቂያ መረጃ

ማንኛውም የምግብ ማስታወቂያ፡-

1. ምግቡን ለማስተዋወቅ የአምራቹን ወይም የአስመጪውን ስም መጥቀስ ይኖርበታል፡፡
2. ማንኛውም በቴሌቪዥን የሚተዋወቅ ምግብ ማሸጊያ ላይ ያለው ገላጭ ጽሁፍ በግልጽ ለእይታ መቅረብ አለበት፡፡
3. የምግቡ ይዘትና ጥቅም የሚገልጽ ከሆነ በባለስልጣኑ ወይም በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡
4. አለርጂ ወይም የደም ግፊት ወይም ስኳር ወይም ቅባት ወይም ሌሎች ተያያዥ ችግር ያለባቸው ሰዎች ሊጠቀሙ የማይችሏቸውን ምግቦች ወይም ማድረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄ መገለፅ አለበት፡፡

7. ስለ አጠቃላይ ክልከላ

1. ማስታወቂያው ጤናማና የተመጣጠነ የአመጋገብ ስርዓትን የሚቃረን መሆን የለበትም፡፡
2. በትክክለኛ ሰነድና በመረጃ ያልተረጋገጠ እንደ “ብቸኛ”፣ “ለመጀመሪያ ጊዜ”፣ “ከዚህ ቀደም ያልነበረ”፣ “የሁሉም ምርጫ”፣ “ለሁሉም ተስማሚ”፣ “ልዩ”፣ “አንደኛ”፣ “ተቀባይነት ያገኘ” ወይም ሌላ መሰል የተጋነነ አበላላጭ ይዘት ያለውን ቃል ወይም ምስልን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡
3. ባለስልጣኑ የተመዘገቡ ወይም የተፈቀዱ የሌሎች ታዋቂ ድርጅቶችን የንግድ ምልክት፣ ብራንድ፣ ስም፣ አርማና ሌሎች ተመሳሳይ ቃላትን መጠቀም አይቻልም፡፡

4. ምግቡ ካለው ባህሪይ የተለየና አሳሳች ባለው ይዘት መልኩ ኦርጋኒክ ሳይሆን ኦርጋኒክ ወይም ኮሌስትሮል እያለው ነጻ ወይም አርቴፊሻል ሆኖ ተፈጥሮአዊ ጣእም እንዳለው አድርጎ በቂ የሆነ ማስረጃ ካልኖረ በስተቀር ማስተዋወቅ አይቻልም፡፡

5. ከፍተኛ የስኳር ወይም የጨው ወይም የቅባት መጠን ያለውን ምግብ አነስተኛ መጠን እንዳለው፣ ነፃ ወይም ለጤና ተስማሚ እንደሆነ በማስመሰል ከመጠን በላይ እንዲጠቀሙ የሚገፋፋ መሆን የለበትም፡፡

6. ምግቡ በሽታን እንደሚያክም ወይም እንደሚያድን መግለጽ የለበትም፡፡

7. በባለስልጣኑ ወይም በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል በተረጋገጠ ማስረጃ ካልተደገፈ በስተቀር ምግቡ በገንቢ፣ በበሽታ ተከላካይና በሃይል ሰጪ ምግቦች ይዘቱ ከፍተኛ፣ የበለጸገ፣ የተሞላ እና ተመሳሳይ የሆኑ ቃላቶችን በመጠቀም ማስተዋወቅ አይቻልም፡፡

8. አጋዥ መረጃዎች፣ ሽልማቶችና ሌሎች ሰነዶች ስለ መጠቀም

1. ድርጅቱ ከምግቡ ጥራት እና ደህንነት ጋር በተያያዘ የተሸለማቸውን ማንኛውም ዓይነት ሽልማቶች በማስታወቂያው ላይ የሚገለፅ ከሆነ ወቅታዊ ማስረጃ ሊኖረው ይገባል፡፡

2. የምርምር እና ሳይንሳዊ ውጤትን በባለስልጣኑ ወይም በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ያለው ሳይረጋገጥ ማስተዋወቅ የተከለከለ ነው፡፡

3. የላብራቶሪ ውጤቶችን፣ የምርመራ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መረጃ በባለስልጣኑ ወይም በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ሳይረጋገጥ በማንኛውም መንገድ ቢሆን ለማስታወቂያነት መጠቀም አይቻልም፡፡

4. ማንኛውም ከፍተኛ የስኳር*፣ ጨው*፣ ቅባት* ወይም ሌላ የሰውን ጤና ሊጎዱ የሚችሉ ንጥረ ነገር የያዙ ምግቦች ለማስተዋወቅ እንደ ሽልማት፣ ስጦታ ወይም በሌላ መልኩ ምግቡ እንዲሸጥ የሚገፋፉ ማበረታቻ ነገሮች መጠቀም አይቻልም፡፡ (*በአዝል 1 ስር ይመልከቱ)

## ክፍል ሶስት

## ስለ ጨቅላ፤ ታዳጊ ህጻናትና ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ምግብ ማስታወቂያ

9. ስለ ጨቅላ ህፃን ምግብ ማስታወቂያ

1. ማንኛውም የጨቅላ ህፃን ምግብ በመገናኛ በብሮድካስት አገልግሎት ማስተዋወቅ የተከለከለ ነው፡፡

2. ማንኛውም ሰው የጨቅላ ህፃንን ምግብ ሽያጭ ለማስተዋወቅ ሲባል ለእርጉዝ ሴቶች፣ ለጨቅላ ህፃናት እናቶች ወይም ለቤተሰብ አባል የጨቅላ ህፃን ምግብ ናሙና ወይም ስለ ምግቡ የሚገልፁ ማንኛውም ዓይነት ስጦታ፣ እቃ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ነገር መስጠት የተከለከለ ነው፡፡
3. ማንኛውም የጨቅላ ህፃናት ምግብ የሚሸጥበት፣ በነጻ የሚሰራጭበት ጤና ተቋም፣ ሱፐር ማርኬት ወይም ልዩ ሱቅ ስለ ምግቡ ጠቀሜታና አስፈላጊነት ሊያሳይ ወይም ሊገልፅ የሚችል የተጋነነ ምስል ወይም ሌላ ፅሁፍ መለጠፍም ሆነ ምግቡን በቀጥታ ሰው እንዲገዛው ለማነሳሳት እንደ ናሙና መስጠት፣ "የዋጋ ቅናሽ" ወይም "የማጣሪያ ሽያጭ" የሚሉ መልእክቶች መለጠፍ ወይም ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡፡
4. በጤና ባለሙያዎች ጤና ተቋማት ውስጥ በሚደረግ ማስታወቂያ የእናት ጡት ወተትን እንደሚተካ፣ እንደሚሻል ወይም እንደሚበልጥ ማስተዋወቅ አይቻልም፡፡

10. ስለ ታዳጊ ህጻናት ምግብ ማስታወቂያ

1. ማንኛውም የታዳጊ ህጻናት ምግብ ማስታወቂያ ምግቡ ከእናት ጡት ወተት በተጨማሪነት እንደሚሰጥ መግለጽ አለበት
2. ምግቡ በሽታን እንደሚያክም ወይም እንደሚያድን መግለጽ የለበትም
3. ማንኛውም የታዳጊ ህፃናት ምግብ ስለ ምግቡ ጠቀሜታና አስፈላጊነት ሊያሳይ ወይም ሊገልፅ የሚችል የሚገፋፋ የህጻናት ወይም የእናቶች ምስል ወይም ሌላ ፅሁፍ በማስታወቂያው ላይ መኖር የለበትም፡፡
4. ማስታወቂያው ህጻናትን ተዋናይ አድርጎ የሚጠቀም ወይም ሌላ መሰል መልእክት የሚያስተላልፍ መሆን የለበትም፡፡

11. ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅን ስለሚመለከት የምግብ ማስታወቂያ

ማንኛውም ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን መሰረት አድርጎ የሚሰራጭ ማስታወቂያ፣

1. የተዋወቀውን ምግብ የተጠቀመ ልጅ ምግቡን ካልተጠቀመ ልጅ በላይ የአካላዊ፣ የማህበራዊ ወይም አእምሯዊ ጠቀሜታ ወይም ብልጫ እንዳለው የሚገልጽ መሆን የለበትም፡፡
2. ለአካለመጠን ላልደረሰ ልጅ ተብሎ ባልተዘጋጀ የምግብ ማስታወቂያ ላይ ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅን ቃል፣ ሀረግ፣ ስም ወይም ምስል የሚያሳይና ሌላ መሰል ይዘት ወይም አቀራረብ የያዘ መሆን የለበትም።
3. ወላጆች፣ ሞግዚቶች ወይም አሳዳጊዎች በልጆች ጤናማና የተመጣጠነ የአመጋገብ ስርዓት የሚኖራቸውን የምክርና አስተምህሮ ሚናን አሳንሶ የሚያሳይ መሆን የለበትም፡፡

4. ልጆች ፈጣን ምግብን (Fast Food) በመደበኛና ጤናማ የአመጋገብ ስርዓት ምትክ እንዲመገቡ የሚያበረታታ መሆን የለበትም፡፡

5. ማንኛውም ከፍተኛ የስኳር፣ የጨውና ቅባት መጠን የያዘ ምግብ ለልጆች በተዘጋጀ ፕሮግራም ማስተዋወቅ አይቻልም፡፡

# ክፍል አራት

## ስለ ተጨማሪ ምግቦች ማስታወቂያ

12. የተጨማሪ ምግቦች ማስታወቂያ

1. ምግቡ በሽታን እንደሚያክም ወይም እንደሚያድን መገለጽ የለበትም፡፡

2. ምግቡ ከመጠን በላይ መወሰድ እንደሌለበት መግለጽ ይኖርበታል፡፡

3. በመደበኛነት ከምንመገባቸው ምግቦች በተጨማሪነት መወሰድ እንዳለባቸው መጥቀስ ይኖርበታል፡፡

4. በተፈጥሮ ወይም በመደበኛነት ከምንመገባቸው ምግቦች የሚመረጡ እንደሆኑ ተደርጎ መጠቀስ የለበትም፡፡

5. ለማስተዋወቅ ሲባል ለነፍሰ ጡር፣ የጨቅላ ህፃናት እናቶች ወይም ሌላ በጤና ባለሙያ ትእዛዝ የሚሰጡ ተጨማሪ ምግቦችን በነጻ ወይም በስጦታ መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

6. የሚሸጥበት ፋርማሲ ወይም ልዩ ሱቅ ምግቡን በቀጥታ ሰው እንዲገዛው ሊያነሳሱ የሚችሉ የማስታወቂያ መንገዶችን እንደ ናሙና መስጠት፣ የተለየ የማስታወቂያ ወይም የማሳያ መንገድ መጠቀም፣ "የዋጋ ቅናሽ"፣ "ልዩ" ወይም "የማጣሪያ ሽያጭ" የሚሉ መልእክቶች መለጠፍ ወይም ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡፡

7. እነዚህን ምግቦች ከፋርማሲዎች ወይም ከልዩ ሱቆች ባለሙያ ምክር መወሰድ እንዳለባቸው መግለጽ ይኖርበታል፡፡

# ክፍል አምስት

# ስለ አልኮል መጠጥ ማስታወቂያ

13. ስለ አልኮል መጠጥ ማስታወቂያ

1. ማንኛውም የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያ መጠጡን መጠቀም ለጤና ተስማሚ እንደሆነ፣ ግላዊና ማህበራዊ ስኬትን እንደሚያስገኝ፣ ለተሻለ ሥነ ልቦናዊ ወይም አካላዊ ብቃት እንደሚጠቅም፣ የፈዋሽነት ባህሪ እንዳለው፣ ለግብረ ስጋ ግንኙነት የተለየ ጥቅም እንዳለው፣ የንጥረ ነገሮቹን በጎነት፣ ከመጠን በላይ መወሰድን የሚገፋፋ ወይም መሰል የተጋነነ መልእክት የሚያስተላልፍ መሆን የለበትም፡፡

2. በማንኛውም የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያ የአልኮል መጠጡ በኃላፊነት መጠጣት እንዳለበትና ለአካለ መጠን ላልደረሰ ልጅ የማይሸጥ ወይም የተከለከለ እንደሆነ መግለፅ አለበት፡፡

3. የአልኮል መጠኑ ከ10 በመቶ በላይ የሆነ ማንኛውም መጠጥን የሚመለከት ማስታወቂያ ከውጭ ከሚለጠፍ ማስታወቂያ እና እለታዊና ሳምንታዊ ካልሆነ ጋዜጣ እና መጽሔት በስተቀር በሌሎች የማስታወቂያ ማሰራጫ ወይም ማስተላለፊያ መንገዶች አማካኝነት ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡፡

4. አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ወይም አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅን የማስታወቂያው ተዋናይ አድርጎ የሚጠቀም ወይም ሌላ መሰል መልእክት የሚያስተላልፍ መሆን የለበትም፤

5. የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያ በመገናኛ ብዙሀን ላይ በሚሰራጭ የልጆች ፕሮግራም ላይ ማስተዋወቅ የተከለከለ ነው፡፡

6. ማንኛውም የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያ የልጆች ፕሮግራም ከመጀመሩ ሰላሳ ደቂቃ በፊት እና ካለቀ በሰላሳ ደቂቃ ጊዜ ውስጥ መተላለፍ የለበትም፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

14. በስፖንሰር ስለሚቀርብ ማስታወቂያ

ማንኛውም በስፖንሰር የሚቀርብ የምግብ ማስታወቂያ ይዘት የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ያከበረ መሆን አለበት።

15. ስለተካታች ማስታወቂያ

ማንኛውም የምግብ ማስታወቂያ አስነጋሪ ወይም አሰራጭ የማንኛውንም ሰው የምግብ ማስታወቂያ በተዘዋዋሪ መልኩ በፅሁፍ፣ በድምጽ ወይም በምስል ከአንድ ፕሮግራም ጋር አካቶ ለማስተዋወቅ ሲፈልግ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ያከበረ መሆን አለበት።

16. ማስታወቂያ አሰራጭ ኃላፊነትና ግዴታ

ማንኛውም የማስታወቂያ አሰራጭ አካል በማስታወቂያ አስነጋሪው ወይም ወኪል የቀረበለትን መረጃ የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች የተከበሩ መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

17. ስለ መረጃ

ማንኛውም የማስታወቂያ አሰራጭ የሚያሰተላልፋቸውን የምግብ ማስታወቂያ መረጃ ከተፈቀደለት በኋላ ቢያንስ ለስድስት ወር ይዞ ማቆየት ይኖርበታል፡፡

18. ስለ አፀፋ ማስታወቂያ

ማንኛውም የማስታወቂያ አስነጋሪ ወይም አስተላላፊ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ከተላለፈ ማስታወቂያ ሲያስነግር ወይም ሲያስተላልፍ ጉዳት የደረሰበት ሰው አፀፋ ማስታወቂያ እንዲተላለፍለት አግባብ ያለውን አካል ሊጠይቅ ይችላል፡፡

19. የመተግበር ግዴታ

ማንኛውም ማስታወቂያ አሰራጭ ወይም አስነጋሪ ወይም ወኪል ሰው የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የመተግበር ግዴታ አለበት፡፡

20. ቅጣት

ማንኛውም ሰው ይህንን መመሪያ ተላልፎ ሲገኝ ዘርፉ የሚመራበት ስለ ምግብ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር የወጣ አዋጅ ቁጥር 661/2002 እና ሌሎች አግባብ ያላቸው ሕጎች መሰረት በሕግ ሊጠየቅ ይችላል፡፡

21. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ ሰርኩላር ደብዳቤ ወይም የአሰራር ልማድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

22. የተሻረ መመሪያ

"የምግብ ማስተዋወቅ ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 5/2004" በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

23. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከታህሳስ ወር 2008 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን**

<u>የንጥረ ነገሮች መጠን (መብለጥ የለበትም)</u>

1. አልኮል............0.08 ግራም በ1 ዴሲ ሊትር ደም ውስጥ
2. ጨው...............5 ግራም በቀን
3. ስኳር...............50 ግራም በቀን ከሚገኘው አጠቃላይ የኃይል መጠን
4. ቅባት...............30 ግራም በቀን ከሚገኘው አጠቃላይ የኃይል መጠን